# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 294 ታህሳስ 18 2006 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ብአዴን የህወሀትን ዙፋን ከመጠበቅ በስተቀር ባለፉት 22 አመታት እወክለዋለሁ ለሚለው ህዝብ ምን ሰራ? ሰፊው የአገራችን መሬት ለሱዳን ተላልፎ ሲሰጥ የስምምነት ፊርማውን ከማስቀመጥ፣ ህዝቡ ከቦታ ቦታ ሲፈናቀል፣ ለአመታት በኤድስና በወባ እንደቅጠል ሲረግፍ፣ ወጣቱ ስራ አጥቶ በአደገኛ እጾች ደንዝዞና ተስፋ ቆርጦ የወጣትነት እድሜውን በከንቱ ሲያሳልፍ ብአዴን የት ነበር? ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ከንቲባ ኩማ ዲሪባ የአዲስ አበባን ነዋሪዎች በልማት ስም ከንዘብ የሚዘርፈበትን ዕቅድ አወጣ

በወያኔው ጉጅሌ ተላላኪ የአዲስአበባ ከንቲባ ድሪባ ኩማ የሚመራው የከተማዋ አስተዳደር በልማት ስም ከነዋሪው ህዝብ ላይ 500 ሚሊዮን ብር በመጫን በሚቀጥሉት ጊዜያት በካድሬዎቹ አማካኝነት ለመሰብሰብ ዝግጅቱን ማጠናቀቁን የወያኔው አፍቃሪ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ። በቅርቡ በጉጅሌው አገዛዝ አገዛዝ ቀጥተኛ ትእዛዝ ወደ ከንቲባነት የመጣው ድሪባ ኩማ ከአለቆቹ በተሰጠው ቀጭን ትእዛዝ አማካኝነት ለመንገድ ለመብራትና ለተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ማከናወኛ በሚል ሽፋን የተለመደውን ዘረፋ አጠናክሮ ቀጥሏል። የከተማዋ ህዝብ በአሁኑ ወቅት በዘረኛ ፖሊሲ በመልካም አስተዳደር እጦትና በሙስና መከራውን እያየና ቤተሰቡን ማስተዳደር ባልቻለበት ሁኔታ ላይ ፋሺስቱ የጉጅሌ አገዛዝ በህዝቡ ላይ የጫነው መዋጮ እጅግ እንዳስመረራቸው የመረጃ አቀባያችን ካነጋገራቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ለመረዳት ችለናል።

የቻይናው የኮንስትራክሽን እና የኢንጂነሪንግ ኩባንያ በጉጅሌው 40 በ60 የቤቶች ግንባታ ላይ ለመሳተፍ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ከወደ አዲስ አበባ የደረሰን መረጃ አመለከተ። ባለፉት 22 አመታት ከጉጅሌው አገዛዝ ጋር እጅና ጓንት በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ተከናወኑ በተባሉት የኮንስትራክሽን እንቅስቃሴ እጅግ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የቻይና ኩባንያዎች ከአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ የሆነ ሙስናና ዘረፋ በማከናወን ላይ መሆናቸው በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል። የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ በማእድን በቴሌኮም በመንገድ እና በሌሎችም የኮንስትራክሽን እንቅስቃሴዎች ላይ ከወያኔ የጦር ጄኔራሎች እና ሲቪል ባለስልጣናት ጋር በመሻረክ ከፍተኛ የሆነ የሀገር ሀብት ዘረፋ ማከናወናቸው በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ተዘግቧል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው አገዛዝ ከገባበት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመውጣት በማሰብ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በቦንድ ግዢና በተለያዩ ዘዴዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ አደረገው ሙከራ በኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ ባለመሳካቱ በቅርቡ 40 በ 60 ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ኦብነግ ከወያኔ ሀይሎች ጋር ተኩስ ተለዋወጠ

የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) ታጣቂ ኃይሎች ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከወያኔ ሰራዊትና ከሶማሌ ክልል ልዩ ሚሊሺያ ኃይሎች ጋር የተኩስ ልውውጥ ማድረጉን የግንባሩ ቃል አቀባይ ይፋ አደረገ። በያዝነዉ የፈረንጆቹ አመት መገባደጃ ላይ የኦብነግ ቃል አቀባይ ለአለም አቀፍ የዜና ማሰራጫ አዉታሮች በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ በተኩስ ልዉዉጡ ወቅት ከሰባ በላይ የወያኔ ወታደሮች እንደተገደሉና ከኦብነግም በኩል የተወሰኑ ታጣቂዎች መሞታቸዉንና መቁሰላቸዉን ገልጿል። ጋዜጣዊ መግለጫዉ ከወያኔ በኩል ሦስት ወታደራዊ አዛዦች መገደላቸዉን አክሎ ገልጿል።

የወያኔ አገዛዝ በቃል አቀበዮቹ በኩልም ሆነ በዜና ማሰራጫዎቹ በኩል ግጭቱን አስመልክቶ ምንም አይነት ዝርዝር መግለጫ ባይሰጥም የሰማሌ ክልል ልዩ ሚሊሺያ ሀይል በወሰደዉ የማጥቃት እርምጃ የኦብነግን ወታደራዊ አዛዥ መግደሉን አገር ዉስጥ ለሚታተሙ ጋዜጣጦች ተናግሯል። ከዚህ በተጨማሪ ደጋሀቡር፣ ቆራሄና ፊቅ ዉስጥ ከኦብነግ ጋር ተባብራችኋላ በሚል የሀሰት ክስ ተከስሰዉ በርካታ ሰዎች ተይዘው መታሰራቸውም ተዘግቧል። የኦጋዴን አካባቢ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የሚፈጸምበት አካባቢ ሲሆን በዚህ አካባቢ የሚደረጉ ወታደራዊ ግጭቶችንም ሆነ ወያኔ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚፈጽመዉን ሰቆቃ፤ እስርና እንግልት የአለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀንም ሆነ የሲቪክ ድርጅቶች ተንቀሳቅሰው መዘገብ አይችሉህም።

የወያኔ አገዛዝ የሶማሌ ክልል ሰለም ሰፍኖባቸዉ ከፍተኛ የልማት ስራዎች ከሚካሄድባቸዉ የአገሪቱ አገካባቢዎች አንዱ እንደሆነ ቢናገርም ከክልሉ የሚደርሱን ዜናዎች ግን ኦጋዴን ከግጭትና ከጦርነት ተገላግላ እንደማታዉቅ ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ወያኔ የዘንድሮዉን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በሶማሌ ክልል ባከበረበት ወቅት በዐሉ ከተከበረበት አካባቢ ብዙም ሳይርቅ የወያኔ ወታደሮችን የኦብነግ ታጣቂዎች ተደጋጋሚ የተኩስ ልዉዉጥ በማድረጋቸዉ በዐሉ ጂጂጋ ዉስጥ የተከበረዉ በከፍተኛ ወታደራዊ አጀብ ተከብቦ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

## ሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤቱን በአስቸኳይ ልቀቅ የሚል ማስጠንቀቂያ ደረሰዉ

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተረፈዉና የወያኔን አገዛዝ ፊት ለፊት በመጋፈጥ ላይ የሚገኘዉ ሠማያዊ ፓርቲ አዲስ አበባ ዉስጥ ግንፍሌ በሚባለዉ አካባቢ የሚገኘውን የፓርቲዉን ዋና ጽ/ቤትበአስቸኳይ ለቅቆ እንዲወጣ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ የተሰጠዉ መሆኑን የፓርቲዉ ቃል አቀባይ ለዜና ማሰራጫ አዉታረዎች በላከዉ መግለጫ ገለጸ። መግለጫዉ አክሎ እንደገለጸዉ አቶ ሄኖክ የተባሉ የሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤት ባለቤት ከኣራት ግለሰቦች ጋር ወደ ጽ/ቤቱ በመምጣት "ቤቱን ለእነዚህ ግለሰቦች ስለሸጥኩት ልቀቁላቸዉ" የሚልና የኪራይ ዉሉን የሚጣረዝ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጥተዋል።

ከአቶ ሄኖክ ላይ ቤቱን ገዝተዋል ከተባሉት አራት ግለሰቦች ዉስጥ አንደኛዉ:-"ቤቱን የኔ ስለሆነ በአስቸኳይ እንድትለቁልኝ፣ ካልሆነ የራሴን እርምጃ እወስዳለሁ" ሲል በሰማያዊ ፓርቲ አመራሮቹ ላይ ዝቷል። ይህ በኪራይ ዉሉ ሰነድ ዉስጥ ስሙ ያልተጠቀሰና ሰማያዊ ፓርቲ በአካራይነትም ሆነ በባለቤትነት የማያዉቀዉ ግለሰብ በማይመለከተው ጉዳይ በመግባት:-" ከዚህ በፊትም ልቀቁ ተብላችሁ በተደጋጋሚ እንደተነገራችሁ መረጃው አለኝ፤ በቶሎ የማትለቁ ከሆነ እርምጃ ይወሰድባችሁዋል" በማለት በአመራሮቹ ላይ ቁጣ የተቀላቀለበት ዛቻ በመዛት ሄዷል:; ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የሙስሊሙ ማህበረሰብ መፍትሄ አፈላላጊ አባላት እስር ቤት ሰቆቃ እንደተፈጸመባቸው ገለጹ

ድምጻችን ይሰማ የሚል ህገ መንግስታዊ የመብት ጥያቄ ስለጠየቁ ብቻ ወያኔ ካያሉበት እየለቀመ ያሰራቸዉ ኢትዮጵያዉያን የእልምና እምነት ተከታይ መሪዎች በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦናዊ እና አካላዊ ስቃይ ደርሶብናል ሲሉ የወያኔን አጋዛዝ አጋለጡ። እነዚሁ በእስር ላይ የሚገኙት የሙስሊሙ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት፣ የደረሱባቸውን በደሎች በዝርዝር እንደተናገሩት:- ከአስራ አራት ሰአት በላይ ያለ እረፍት ቀጥ ብለዉ እንዲቆሙ እንደሚደረጉ፤ ጆርባቸዉን በሽቦ እንደሚገረፉ፤ እጃቸዉ ታስሮና አይናቸዉ በጨርቅ ተሸፍኖ ውስጥ እግራቸዉ ተገልብጦ እንደሚቀጠቀጥና እንቅልፍ እንዳይተኙ እንደሚደረጉ ተናግረዋል;፡ ከዚህ በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ክብራቸዉን በመድፈር ጺማቸዉን እንዲላጩ እንደሚገደዱና ሶላት ማድረስ እንደሚከለከሉም ተናግረዋል።

የአገሪቱ ህግ በሚያዝዘዉ መሰረት ለሌሎች እስረኞች የሚደረገዉ የ ቤተሰብ ጥየቃ፣ በጠበቃ መጎብኘት፤ የህክምና እርዳታ ማግኘትና ከሀይማኖት አባት ጋር መገናኘት እንደማይችሉም ተናግረዋል። እስረኞቹ ጧትና ማታ ከአቅም በላይ የሆነን ስፖርት በግድ እንደሚሰሩ፤ ብልታቸዉን እንደሚቀጠቀጡና፣ ልጅህን እንገለዋለን! ሚስትህን አስረን ፊትህ ቶርች እናደርጋታለን! ብልትህን ቀጥቅጠን ማህን እናደርግሀለን" የሚሉ ማስፈራሪያዎች በየቀኑ እንደሚደርሱባቸዉ ተናግረዋል።

በህገመንግስቱ አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 1 "ማንኛውም ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው" ቢልም፣ እኛ ግን" ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ አገዛዝ የአንድ ለአምስት አደረጃጀትን ወደ ቤተሰብ ማዉረዱ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የዘረኝነት ፖሊሲዉን ለማስረጽና ዜጎች እርስ በርሳቸዉ አንዱ ሌላዉን እየሰለለ በዘለዓለማዊ የፍርሃት ድባብ ዉስጥ እንዲኖሩ ለማድረግ የዘረጋዉን የአንድ ለአምስት አደረጃጀት ወደ ቤተሰብ ደረጃ ለማዉረድ ያወጣዉን ዕቅድ ተግባራዊ በማድረግ ላይ መሆኑን ከወደ ኢትዮጵያ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ወያኔ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ፣ በትምህርት ቤቶች ፣ በአርሶ አደሩና በከተማው ነዋሪዎች ላይ ሲዘረጋ የቆየውን የአንድ ለአምስት አደረጃጀት በቤተሰብ ደረጃ ለማዋቀር የተለያዩ ደብደቤዎችን እየበተነ መሆነ በመነገር ላይ ነው።

የቦሌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ለወረዳ 02 የቤተሰብ አባላት ባዘጋጀው የቤተሰብ ማቋቋሚያ ቅጽ ላይ የቤተሰብ ፖሊስ መመስረት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት " በቤተሰብዎ መካከል ለሚፈጠሩ የጸጥታ ችግሮች ማለትም ያለመግባባቶች፣ የተለያዩ ማህበራዊ ግችቶች ወዘተ የመሳሰሉት ችግሮች ሲፈጠሩ እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ ወኪል እንደ ፖሊስ ሆኖ በቅርበት ከፖሊስ ጋር እየተወያየ የማስታረቅ፣ የማስማማት ስራ እንዲሰራ እና ችግሩን እየተከታተለ እዛው መፍትሄ እንዲሰጥና መፍታት ያልተቻለ በአካባቢው ከተመደቡት የፖሊስ አባላት ጋር ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ ነው" ይላል። " ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ትግሉ የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅበት ወሳኝ ምእራፍ ላይ ደርሷል

ራሱን የብሄረ አማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ብሎ የሚጠራው ድርጅት በከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ውስጥ ገብቷል። የህወሀትን ዙፋን ከመጠበቅ ባለፈ ምንም ሚና የሌላቸው የብአዴን አመራሮች ያለፉትን ሶስት ወራት በተለያዩ መንገዶች የድርጅቱን አባሎች ሲገመግሙ ከርመዋል። በግምገማዎች ላይ በግልጽ እንደታየው ብአዴን በክልሉ ከሚገኙ ወጣቶች አባሎቹ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኗል፤ ወጣቶቹ በግልጽ "ዙፋን ጠባቂነቱ ይብቃ፣ ለውጥ እንፈልጋለን፣ ብአዴን ለ22 ዓመታት ተፈትኖ የወደቀ ድርጅት ነው" የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተዋል። ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች እየተጫወቱ ያለው ሚና በሌሎች የኢህአዴግ ድርጅቶች ውስጥ ላሉ ወጣት አባላት ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ነው። ሰሞኑን በገሀድ በግምገማዎች ላይ ሲነገር እንደነበረው ብአዴን እወክለዋለሁ ከሚለው የአማራ ህዝብ ሙሉ በሙሉ ተነጥሎ በአየር ላይ የተንሳፈፈ ድርጅት እንዲሆን ወጣቶቹ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ይህን እውነታ ዘግይተው የተረዱት የብአዴን ዙፋን ጠባቂ አመራሮች የሚይዙትን የሚጨብጡትን በማጣት የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ላይ ይገኛሉ። ታማኝ የሚሉዋቸውን ካድሬዎች በየወረዳዎች እና በየቀበሌዎች በመላክ በግንቦት7 አባልነት ወይም ደጋፊነት የሚጠረጠሩትን ወይም የግንቦት7 አባሎች ናቸው ተብሎ ከሚገመቱ ሰዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት አላቸው ተብሎ የሚጠረጠሩትን ሰዎች በመያዝና በማሰቃየት ሌላው ወጣት ተቃውሞውን እንዳይቀላቀል ለማድረግ እቅድ ነድፈው ለመንቀሳቀስ አስበዋል። እንዲሁም አንድ ለአምስት የተባለውን የመጠርነፊያ ስልት በመስሪያ ቤቶች፣ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤቶችና በተለያዩ ተቋማት ላይ በስፋት በማውረድ፣ የህዝቡን የእለት ተለት እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር አልመዋል። የግንቦት7ን ህዝባዊ ሀይል ለመቀላቀል ቆርጦ የተነሳውን ወጣት እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የአካባቢ ፖሊሶችንና የድንበር ጠባቂዎች ሚሊሺያዎችን በማጠናከር እና በማብዛት ለመቆጣጠር ውሳኔ አሳልፈዋል። በድርጅቱ ውስጥ የግንቦት7 ደጋፊዎች ናቸው ተብሎ የሚጠረጠሩትን ወይም ለድርጅቱ ታማኝ አይደሉም የሚባሉትን ሁሉ በመመንጠር ብአዴንን እንደገና በእግሩ ለማቆም ውሳኔ አሳልፈዋል።

በጭካኔያቸው፣ በጎጠኝነታቸው፣ በንቅዘታቸው እና በሎሌነታቸው የሚታወቁትን ታማኝ ካድሬዎች ወደ ፊት በማምጣት ለድርጅቱ እስትንፋስ ለመስጠት ደፋ ቀና እያሉ ነው። ሰሞኑን የተደረገው ሹም ሽርም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም እንደሚባለው የሰዎች መለዋወጥ የብአዴንን ህልውና ከመክሰም አያድነውም።

ለመሆኑ ብአዴን የህወሀትን ዙፋን ከመጠበቅ በስተቀር ባለፉት 22 አመታት እወክለዋለሁ ለሚለው ህዝብ ምን ሰራ? ሰፊው የአገራችን መሬት ለሱዳን ተላልፎ ሲሰጥ የስምምነት ፊርማውን ከማስቀመጥ፣ ህዝቡ ከቦታ ቦታ ሲፈናቀል፣ ለአመታት በኤድስና በወባ እንደቅጠል ሲረግፍ፣ ወጣቱ ስራ አጥቶ በአደገኛ እጾች ደንዝዞና ተስፋ ቆርጦ የወጣትነት እድሜውን በከንቱ ሲያሳልፍ ብአዴን የት ነበር? አንድ የብአዴን ከፍተኛ አመራር በገሀድ እንዳመኑት ድርጅቱ ከህዝቡ ጋር ሳይተዋወቅ 22 አመታት አልፈዋል።

ግንቦት7 መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ከዘረኛውና ዘራፊው የህወሀት ጎጠኛ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገል እና በምትኩ የሁሉም የምትሆን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የጀመረውን ትግል ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ ቀጥሏል። በዚህ ወሳኝ የትግል ምእራፍ ወቅት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተለይም በኢህአዴግ ድርጅቶች ውስጥ ታቅፈው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ እውነተኛ የስርአት ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ ሀይሎች የብአዴን ወጣት አባላት ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ልምድ በመቅሰም በውስጥ የሚያደርጉትን ትግል አጠንክረው እንዲገፉበት ንቅናቄያችን ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## ከንቲባ ኩማ ዲሪባ የአዲስ አበባን ነዋሪዎች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተባለ ዘዴ ዜጎች በብዙ ድካምና ጥረት ያገኙትን ገንዘብ ቤት ሰርቼ አስረክባለሁ በማለት በቅድሚያ ገነዘብ ካሰባሰበ በሁዋላ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ግንባታው እንደሚዘገይና መጀመርያ ከተተመነው ዋጋ በላይ በመጠየቅ ላይ እንደሆነ ለ40 በ 60 የቤት ፕሮጀክት የተመዘገቡና የቅድሚያ ክፍያውን ያጠናቀቁ በአውሮፓና በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች የሚኖሩ ነዋሪዎች በምሬት ሲናገሩ ይደመጣሉ።አንድ ስሟ እንዳይገለጥ የጠየቀች ባውሮፓ ነዋሪ የሆነች ኢትዮጵያዊት እንደተናገረችው በወያኔው 40 በ 60 የቤት ግንባታ ጠቅላላ 560,000 የኢትዮጵያ ብር እንደተጠየቀችና ቅድመ ክፍያውን ካጠናቀቀች ከወራቶች በሁዋላ በኮንስትራክሽን እቃዎች ዋጋ መጨመርና በቂ የመኖርያ ቤት መስሪያ መሬት በከተማዋ ባለመኖሩ ምክንያት ከጠቅላላ ዋጋው በተጨማሪ 200,000 የኢትዮጵያ ብር ጭማሪ ተደርጎ ወደ 760000 ብር ከፍ እንዳለ በምሬት ተናግራለች።በመቀጠልም የተጠየቀውን ጭማሪ ገንዘብ ብትከፍልም ወያኔ ቃሉን አክብሮ ቤቱን ሰርቶ እንደማያስረክባት ከፍተኛ ጥርጣሬ ያላት መሆኑን ገልጻ እንዳትተወው በቅድሚያ የከፈለችውን ገንዘብ ላለማጣት ስትል መወሰን እንዳቃታት ተናግራለች።በሐገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲና የፍትህ አስተዳደር ሳይኖር ንብረት አፍርቶም ሆነ ንብረትን በህግ አስከብሮ የመኖር ዋስትና ባለመኖሩ በቅድሚያ ይህንን በሙስና በቅጥፈትና በማጭበርበር የታጀለ የጉጅሌ አገዛዝ በማስወገድ ዜጎች በሐገራቸው ላይ ንብረት አፍርተው በሰላምና በሕግ ፊት እኩል ሊሆኑ የሚችሉበትን ስርአት ለመፍጠር በሚደረገው ግብግብ የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ ጉዳዩን የታዘቡ አንድ ኢትዮጵያዊ ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል።

## ሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤቱን በአስቸኳይ ልቀቅ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሰማያዊ ፓርቲ ከዚህ ቀደም በመነን አከባቢ ተከራይቶት የነበረውን ጽ/ቤት ገና ሳይገባበት በዝግጅት ላይ እንዳለ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና እና ቅጥረኞች በተቀናጀ አፈናና ሀይል የተቀላቀለበት እርምጃ ቢሮውን እንዳስለቀቁት ይታወቃል። ቀደም ሲል ከሰማያዊ ፓርቲ የተነጠቀውን ቢሮ የወሰደው ካድሬም፤ ፔንሲዎን ከፍቶ እየነገደበት እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።የፓርቲው ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ ፓርቲያቸውን በውጪ አገራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በማስተዋወቅ ላይ እንደሚገኙ የሚታወቅ ሲሆን ገዢዉን ፓርቲም ያሰበረገገዉና እንዲህ አይነት ፓርቲዉን ያለ ጽ/ቤት እንዲቀር የሚያደርግ እርምጃ እንዲወስድ ያስገደደዉ ይሄዉ ሠማያዊ ፓርቲና መሪዎቹ አገር ዉስጥና ካገር ዉጭ ተወዳጅ እየሆኑ መምጣታቸዉ ነዉ።

## የሙስሊሙ ማህበረሰብ መፍትሄ አፈላላጊ አባላት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዜጎች መሆናችንን ጥርጣሬ ውስጥ በሚከት መልኩ ከያዙን በሁዋላ በማእከላዊ በክረምት ቀርቶ በበጋ እንኳን ቅዝቃዜው በማይቻለው “ሳይቤሪያ” ተብሎ በሚጠራው ጨለማ ክፍል ለ3 ዋር አገሩው መቋቋም የሚአዳግተውን የማሰቃያ ስልታቸውን በመጠቀም አላሰብነውንና ያልሰራነውን“እመኑ! ተናገሩ! ፈርሙ! ብለው አስገድደውናል” ሲሉ በመግለጫቸው ጠቀስዋል።

ፍርድ ቤት ስቃዩን እንዲያስቆምልን ብንጠይቅም፣ ያገኘነው ውጤት ግን ወደ ማእከላዊ ስንመለስ ከመርማሪዎቹ በቀልና ተጨማሪ ስቃይ ነበር፣ የሚሉት ኮሚቴዎቹ፣ አሰቃዮቻችን ስለህገመንግስቱ እና መብት ስንናገር ” ህገ-መንግስቱን ቀደህ ጣለው፣ እኛ መስዋትንት ከፍለን ነው እዚህ የመታነው በማለት ለህግም ሆነ ለሰው ክብር ዴንታ እንደሌላቸው አሳይተውናል” ሲሉ አክለዋል።ከቤተሰብ፣ ከጠበቃና ከሀኪም ጋር እንዳንገናኝ አድረገው የፈጸሙብን የህግ ጥሰት እና አስገድደው በማስፈረም እና ድምጽና ምስላችንን በመቅረጽ የፈጸሙብን በደል በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 424 መሰረት እስከ አስር አመት የ አስቀጣ ኢ-ሰብአዊ ተግባር ቢሆንም የፖሊሱም፣ አቃቢህጉም ፣ የፍርድ ቤቱም አለቃ በሆነውና የፍትህ ስርአቱን ሰብስቦ በያዘው ገዢው ፓርቲ አምባገነንነት በተቃራኒው እኛ ተከሳሽ ሆነን ጉዳያችን በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ይገኛል ብለዋል።

መንግስት በአግባቡ ሊተውነው ያልቻለውን አሳፋሪ የፍርድ ቤት ድራማውን ህዝብ እንዳያይበት ለመሸሸግ በመገደዱ የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በሁዋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለህዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመስማት መብት አላቸው የሚለውን ህገመንግስታዊ መብት በመጣስ ችሎቱ ዝግ እንዲሆን ተደርጎ ቆይቷል የሚሉት የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት፣ በዝግ ችሎቱ የምስክር መስሚያ ጊዜ ብዙ አስገራሚ ድራማዎችን አይተናል፣ አቃቢ ህግ ዳኞች የሚሰጡትን ብይን እንደማይቀበሉ እስከመግለጽ የደረሱበትን እና ምስክሮችን ማለት ያለባቸውን አሰልጥነዋቸው እንደሚያመጡ አምልጧቸው የተናገሩበትን አጋጣሚ ”መታዘባቸውን ይገልጻሉ። የኮሚቴው አባላት” በሙስሊሞች መካከል እና በሙስሊሙና በክርስቲያኑ መካከል የታየውን አንድነትና መከባበር በጋራ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ መክረዋል። በጽናት ሰላማዊ የመብት ትግሉን የሚቀጥሉ መሆናቸውንና የሚያስከፍለውን መስዋትንት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውንም ተናግረዋል። ለቀጣዩ ሰላማዊ የመብት ትግል እርከንም በሙሉ ዝግጅት ላይ መሆናቸውን” ገልጸው፣ መንግስት በማእከላዊ እስር ቤቶች የሚፈጸሙትን ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች እንዲያስቆምና የህሊና እስረኞችን እንዲለቅ ጠይቀዋል።

## ይድረስ ለብአዴን አባላት

በረከት ስምዖንና አዲሱ ለገሰ ወደ ባህር ዳር አቅንተው ነበር። መቸስ በረከት ስምዖን አማራ ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ አለመንደሩ የአማራ ህዝብ መሪ እኔ ነኝ ብሎ ከአማራ ህዝብ ፊት ሲቆም አለማፈሩ ያስገርማል። አዲሱ ለገሰም እንደ በረከት ራሱን የአማራ ህዝብ ወኪል እኔ ነኝ ይላል።እነዚህ ሁለት ህወሃት የሠራቸው ፍጡራን ባህር ዳር እንዲወርዱ ያደረጋቸው ብአዴን ተዳክሟል ተብሎ መታሠቡ ነበር።

እንግዲህ በእነበረከት የአስተሳሰብ ደረጃ ብአዴን ተዳከመ ሲባል ምን ማለት ይሆን?

ከጥቂት ደካማ ካድሬዎች በቀር ሌሎች እንደ ሰው ማሰብ የሚችሉ የብአዴን አባላት አገሪቷ እየሄደች ያለችበት መንገድ ያሳስባቸዋል። ህወሃት በአማራ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ የሚያንገበግባቸው በርካታ ናቸው። ጉርፋርዳ እና ቤንሻንጉል አገራችሁ አይደለም ተብለው አማሮች ከኖሩበት ቀየ ተፈናቀለው ሜዳ ላይ የመውደቃቸው ድርጊት የእግር እሳት ሁኖ የሚለበልባቸው ብዙዎች አሉ። በዚህ ሁኔታ ያዘኑና የተቆጡ የብአዴን ካድሬዎች ድርጅቱ ቆሜለታለው የሚለው ፍትህ የት አለ፤ እኩልነትስ ከወዴት አለ፤ ኢትዮጵያስ የሁላችን አገር ነች የምትባለው መገለጫው ምንድ ነው እያሉ ይጠይቃሉ። እነዚህ ጥያቄዎች በካድሬዎች መካከል መመላለስ ሲጀምሩ ድርጅቱ ተዳክሟል ተብሎ ግምገማ ይካሄዳል።

በረከት እና አዲሱ ነፃነትን ሳያውቁ ራሳቸውን ነፃ አውጪ አድርገው የሚቆጥሩ የህወሃትን ዙፋን ከመጠበቅ የዘለለ ምንም ሚና የሌላቸው ያልሆኑትን ለመሆን የሚውተረተሩ ደካሞች መሆናቸውን እናውቃለን። እነዚህ ግለሰቦች ስለ አማራ ህዝብ ነፃነትና ክብር ይሠራሉ ብሎ ማሰብ የሚቻልበት ሁኔታ የለም። በረከትና አዲሱ በህዝብ መካከል እየኖሩ የህዝብ ፍቅር የሌላቸው፤ ከህዝቡ ጋር መኖርንም የማያውቁ፤ እለት ዕለት በሚፈጥሩት የፍርሃት አረንቋ ውስጥ የሚኖሩ እና ሠላም የራቃቸው ግለሰቦች ናቸው። ከእነዚህ ግለሰቦች እውነትን ፈልጎ ማግኘት፤ ነፃነትን ጠይቆ መቀዳጀት፤ ለፍትህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት የሚቻል አይደለም። የአማራ ህዝብ ከጉራፋርዳ እንዲወጣ የተደረገበት ምክንያት ምንድ ነው ተብለው ሲጠየቁ የጠባቦች ጥያቄ ብለው ይሳደባሉ። አያቶቻችን በደምና አጥንታቸው ያቆዩልንን ድንበር አፍርሳችሁ ለባእዳን ለምን ትሰጣላችሁ ሲባሉ የጦርነት ናፋቂ ጥያቄ እያሉ ይዘባበታሉ። እንደምን ሁኖ ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማራ ከቁጥሩ ጎድሎ ተገኘ ሲባሉ የትምክህተኞች ወሬ እያሉ ይሳለቃሉ። አዎን እነበረከት ስምዖን የሚፈልጉት ዜጎች ስድባቸውን ተሸከመው እንዲኖሩላቸው እንጂ እውነትን፤ ፍትህን እና እኩልነትን እንዲጠይቁ አይደለም።

የሰሞኑ የባህር ዳር አስቸኳይ ስብሰባ ምክንያትም በብአዴን ካድሬዎች መካከል የፍትህ፤ የነፃነት እና የእኩልነት ጥያቄዎች ሥር እየሰደዱ መምጣታችው ነው። በካድሬዎቹ መካከል እንደ እሳት ሰደደ እየተሰራጬ ላሉ የፍትህ፤ የነፃነት እና የእኩልነት እጦት ጥያቄዎች ከህወሃት መራሹ "መንግስት መሰል" አካል በቀላሉ መልስ ማግኘት የሚቻል አይደለም። ይሄ ቡድን ነፃነትን ሳያውቅ ነፃ አወጣኋችሁ ማለትን ብቻ የሚያውቅ፤ራሱ ለሠራው ህግ መገዛትን ሳይወድ ስለ ህገ-መንግስት የበላይነት የሚሰብክ፤ ራሱ ከሁሉ በላይ እኔ ነኝ ብሎ ሲያበቃ ስለ እኩልነት ለመስበክ የማያቅማማ የነውረኞች ስብሰብ ነው። በረከትና አዲሱም የዚህ ነውረኛ ቡድን አካል እንጂ የአማራ ህዝብ አካል ናቸው ለማለት ለአማራ ህዝብ የሠሩት በጎ ነገርን ፈልጎ ማግኘት አይቻልም።

የብአዴን ካድሬዎች ሆይ !

ብአዴን ከተመሠረተ በኋላ ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማራ መጥፋቱን በፓርላማ ሪፖርት መደረጉን ሰምተችኋል።ለመሆኑ ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማራ የት ጠፋ? በአገሪቷ ካሉ ብሄረ ብሄረሰቦች መካከል እንደምን ሁኖ የአማራ ቁጥር ብቻ ሊቀንስ ቻለ? ከአማራ ክልል ወጥተው በሌላ ክልል የሚኖሩ አማሮች ይሄ አገራችሁ አይደለም፤ ወደ አገራችሁ ሂዱ ተብለው የሚባረሩት ለምንድ ነው? ኢትዮጵያ አገራቸው ካልሆነች የእነዚህ አማሮች አገር ወደየት አለች? ከጉራፈርዳ እና ከቤንሻንጉል ተነቅለው ሜዳ ላይ እንዲወድቁ የተደረጉ አማሮች በደላቸው ምንድ ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች አማራ ካልሆንን ሞተን እንገኛለን የሚሉት በረከት ስምዖንና አዲሱ ለገሰ መልስ አይሰጡም። እነርሱ የቆሙት በህወሃት *"የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት አማራ ነው"* ተብሎ የተያዘውን እምነት በተግባር ለማስፈፀም እንጂ ለአማራ ህዝብ ደህንነት እንዳለሆነ ምግባራቸው ህያው ምስክር ነው።

ብአዴን ከተመሠረተ ዘመን ጀምሮ በአማራ ህዝብ ላይ የደረሰውን ግፍ እናውቃለን። የአማራን ቅስም መሰበር፤ ትምክህቱን ማስተንፈስ፤ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ማዋረድ የሚሉት የእነበረከት ስምዖን ዋነኛው መፈክሮቻቸው ናቸው።በዚህ መፈክር መሪነት ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማሮች ጠፍተዋል፤ኢትዮጵያ አገራችሁ አይደለችም ተብለው ከጉራፈርዳ እና ከቤንሻንጉል ውጡ ተብለው ሜዳ ላይ ተጥለዋል። ከንግዱ አምባም ሳይቀር ቀስ በቀስ አማሮች እንዲጠፉ ተደርገው ሥፍራቸውን ለሌላ እንዲለቁ ሁነዋል። ከፕሮፌሰር አሥራት ጀምሮ ለአማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምልክት እና ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አማሮች ቀስ በቀስ እንዲጠፉ መደረጋቸውን በአይናችን አይተናል በጆሮአችንም ሰምተናል። ብአዴን የተባለው ድርጅት በአማራ ስም ቢቋቋምም አማሮችን ከውርደትና ከሚደርስባቸው በደል ሊታደጋቸው አልቻለም።እንዲያውም ግፉንና በደሉን ለማስፈፀም የተወከለ ድርጅት ሁኗል።

እንግዲህ የብአዴን ካድሬዎች ሆይ እናንተም ከበረከተ ስምዖንና ከአዲሱ ለገሰ ጋር ተሰልፋችሁ ህዝባችሁን ትወጉ ዘንድ አይገባም። ዙሮ መግቢያችሁ ዛሬ እንወክለዋለን ያላችሁት ግን ደግሞ በአሣር በመከራ ውስጥ ያለው ህዝብ እንጂ ሌላ ዙሮ መግቢያ እንደሌላችሁ እወቁ። የወከላችሁት ህዝብ ሲረገጥ የለም ህዝቤን አትበድሉ ማለት ይጠበቅባችኋል። አማራ ከቁጥሩ ጎደለ ሲባል ምን ሆኖ እንደጎደለ በመጠየቅ የችግሩን ምንጭ ማወቅ ሥራችሁ ነው። አማራ ወደ "አገርህ" ሂድ ተብሎ ከኖረበት ሲነቀል ኢትዮጵያ አገሩ ካልሆነች የአማራ አገሩ የት ነው ብላችሁ መጠይቅ አለባችሁ።

ዛሬ እናንተን ትምክህተኞች እያለ የሚገመግማችሁ በረከት ስምዖን አያሌው ጎበዜን አስነስቶ ገዱ አንዳርጋቸው እንዲተካ አድርጓል። የአያሌው መሄድና የገዱ መምጣት ለአማራ ህዝብ ነፃነት እና ክብር የሚፈይደው አንዳችም ቁም ነገር የለም። አያሌውም ሆነ ገዱ ለቆሙለት ህዝብ ይቅርና ለራሳቸውም ክብር የሌላቸው ደካሞች መሆናቸው የታወቀ ነው። ለራሱ ክብር ያለው የህዝብ ወኪል እወክለዋለው የሚለው ህዝብ ከኖረበት ቀየ እየተነቀለ ሜዳ ላይ ሲጣል አይቶ ዝምታን አይመርጥም። አያሌውና ገዱ ከአማራ ህዝብ አብራክ ወጥተው ደሃውን አማራ በሙሉ ነፍጠኛ፤ ትምክህተኛ፤ ሌላም ሌላም እያሉ እየሰደቡ ለሳዳቢ አሳላፊው የሰጡ ደካሞች ናቸው። ካድሬ ሆይ ስማን! የገዱ በአያሌው መተካት የተዋረደውን ክብርህን አይመልሰውም። ያጣኸውን ነፃነት መልሶ አያቀዳጅህም። ለሱዳን ተቆርሶ የተሰጠውን በአያቶችህ ደምና አጥንት የቆየውን መሬትም አይመልስልህም። የብአዴን ካድሬዎች ሆይ ስሙ ለክብራችሁ፤ ለማንነታችሁ፤ ለነፃነታችሁ ቀናዒ እንድትሆኑ ሁኑ እንጂ የህወሃትን ትርፍራፊ የምትለቃቅሙ አትሁኑ።

በብአዴን ውስጥ ያላችሁ የንቅናቄያችን አባሎች ሆይ !!

የህወሃት ስንቅና ትጥቁ ጥላቻ መሆኑን ታውቃላችሁ። ህወሃት "አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው" ብሎ የሚያምን ቡድን ነው። ከዚህ ቡድን ፍትህ፤ እኩልነትና ነፃነት ያለመስዋእትነት እንደማይገኝ መዘንጋት አያስፈልግም። እስከ አሁን የንቅናቄያችንን መሠረት ለማሲያዝ ያደረጋችሁት አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በህወሃት የተነጠቀው ነፃነታችን፤ የተዋረደው ክብራችንና ማንነታችን በቀላሉ እንደማይመለስ መገንዘብ ይኖርብናል። ትግሉ መራራ የሚሆንበት ግዜ መጥቷል። ለነፃነትና ለማንነት የሚከፈል መሥዋእትነት ደግሞ አስፈላጊ መሥዋዕትነት ነው።ጥቂት ዘረኞች አንገታችንን አስደፍተው በማንነታችን ላይ ተሳልቀው፤ ህዝባችንን አጎሳቁለውና ረግጠው ሲገዙ በአይናችን እያየንና በጆሮአችን እየሰማን ተንጋለን ለመተኛት አልተፈጠርንም። እንዲህ ዓይነቱን ሥንፍና ከቀደሙት ከኩሮዎቹ አያቶቻችንና አባቶቻችን አልተማርንም።

በአውሬው መረብ ውስጥ ሁናችሁ የለውጥ ኃዋሪያ ለመሆን መነሳታችሁ የሚደነቅ ነው።የለውጥ ኃዋሪያነት ትልቅ ሸከም ያለው ነው።ጥላቻን ወደ ፍቅር የሚቀይር፤ ለይቅርታ ራስን ማዘጋጀት፤ ከግዜያዊ ጥቅም ይልቅ ትውልድን አሻግሮ የማየት ራዕይን የሚጠይቅ ነው። ህወሃት አገሪቷን እያፈረሰ ያለው ከፍቅር ይልቅ በጥላቻ ስለተሞላ፤ ከይቅርታ ይልቅ በበቀል ልቦና የሚመላለስ በመሆኑን፤ ትውልድን አሻግሮ ከማየት ይልቅ የስግብግብነት ስሜቱ ያየለበት ሆኖ በመገኘቱ ነው። ንቅናቄያችን ይህን ከመሰለ አገር አጥፊ አስተሳሰብ በላይ ነው። ንቅናቄያችን ሁል ግዜ ለይቅርታ የተዘጋጀ ልቦና አለው። ይሄ ሲባል ግን የበቀለኞችን ሠይፍ ለመመከት ራሱን አያዘጋጅም ማለት አይደለም። እንዲያውም ሰይፋችን ከእነርሱ ሠይፍ በላይ የሳለ መሆኑን ያውቁት ዘንድ እንወዳለን። ንቅናቄያችን ትውልድን አሻግሮ የሚያይ ባለ ረዥም ራዕይ ነው። እንደ ህወሃት ለዘረፋ የተሠለፈ፤ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል የሚል አይደለም። ዘራፊውንና እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይበቀል የሚለውን ሁሉ ነቅሎ ሥፍራውን ለማስለቀቅ ሳያቅማማ በፅናት የሚሠራ ነው።

በብአዴን ውስጥ ያላችሁ የንቅናቄው አባላት ሆይ!!

የገዱ በአያሌው መተካት የሚያመጣው ለውጥ የለም።አያሌው ሄደ ገዱ መጣ ሁለቱም ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ደካሞች ናቸው። ገዱ የነፃነትን፤የፍትህንና የእኩልነትን ዋጋ የሚያውቅ አይደለም። ገዱ ሲሊኩት ወደየት፤ ሲጠሩት አቤት ከማለት የዘለለ ለዚያች አገር ለውጥ የሚፈይደው አንዳችም ነገር እንደማይኖር እወቁ። ስለሆነም የተጀመረውን ትግል ከዳር ለማድረስ ሳታቅማሙ በፅናት ቁሙ። ፍርሃትን ግደሉት። ከፍርሃት አርነት የሚያወጣን ነፃነት፤ ፍትህና እኩልነት ብቻ ነው። እነዚህ ለሰው ልጆች መሠረታዊ ቁም ነገሮች በአገሪቷ ሰፍነው ዜጎች ሁሉ እፎይ እስከሚሉ ድረስ የሚከፈለውን መሥዋ ዕትነት ለመክፈል ወደ ኋላ እንዳትሉ። በእኛም በኩል አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ለመክፈል የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። የጀመርነውንም ትግል ሳናቅማማ እና ሳናፈገፍግ እንቀጥላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ደቡብ ሱዳን ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አድኑን እያሉ ነዉ

በቅርቡ ከሱዳን ተላይታ የራሷን መንግስት በመሰረተችዉ ደቡብ ሱዳን ዉስጥ በፕሬዚዳንቱና በምክትል ፕሬዚዳንቱ ደጋፊዎች መካከል የተቀሰቀሰዉ ግጭት አገሪቱን ወደ እርስ በርስ ጦርነት እየወሰዳት መሆኑን ከዋና ከተማዋ ከጁባና ከአጎራባች አገሮች የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ይህንን ግጭትና አስመልክቶ ብዙ አገሮች ዜጎቻቸዉን ከጦርነት ቀጠናዉና ባጠቃላይ ከደቡብ ሱዳን በማስወጣት ላይ ሲሆኑ የኢትዮጵያዉያኑ ጉዳይ ግን የሚደርስላቸዉና እርዳታ የሚሰጣቸዉ መንግስት ባለመኖሩ እጅግ በጣም አሳዳቢ ሁኔታ ላይ መድረሱን ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱን መረጃዎች ያስረዳሉ። ደቡብ ሱዳን ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ የእርስ በርስ ግጭት በአገሪቱ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ደህንነት ሁኔታ አሳሳቢ ቢሆንም መንግስት እስካሁን ድረስ ምንም የወሰደዉ ወይም እወስዳለሁ ያለዉ እርምጃ አለመኖሩ ታዉቋል።

ጁባ ዉስጥ የሚገኙት የኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን ምንጮች እንደገለጹት አብዛኛው አገሮች ዜጎቻቻውን እያወጡ ነው። ኬንያና ኡጋንዳ አውቶቡሶችን በመላክ፣ አሜሪካና እንግሊዝ ደግሞ ወታደራዊ አውሮፕላኖችን በመላክ ዜጎቻቻውን እያወጡ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነ አውሮፕላን ጁባ ማረፉን ተከትሎ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ለመመለስ ተስፋ አድርገው የነበረ ቢሆንም፣ አውሮፕላኑ ግን ቻይናዎችን ብቻ ጭኖ መመለሱ ታውቋል። ኢሳት ከአየር መንገዱ ለማረጋገጥ እንደቻለው የቻይና መንግስት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ቻርተር አውሮፕላን በመከራየት በነዳጅ ማውጣት ስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎቹን ወስዷል።

እንዲሁም ለሽምግልና ጁባ የሄዱትን የኢትዮጵያን ባለስልጣናት በማሳፈር ጁባ ያረፈ አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን፣ ባለስልጣኖችን ካወረደ በሁዋላ ትኬት ቆርጠው ለመውጣት ይጠባበቁ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ሳይጭን ባዶውን ተመልሷል። ኢትዮጵያውያኑ የኬንያንና የኡጋንዳን አየር መንገዶችን ለመጠቀም ጥረት እያደረጉ ቢሆንም፣ አየር መንገዶቹ ከፍተኛ ዋጋ በመጠየቃቸው ትኬቶችን ለመግዛት አልቻሉም።

የኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ጅቡቲ እና ሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ላለፉት ሁለት ቀናት በጁባ ተገኝተው ሁለቱን ሀይሎች ለመሸምገል ጥረት እያደረጉ መሆኑም ታውቋል። ደ/ር ቴዎድሮስ አድህኖም ሁለቱንም ሀይሎች ለማቀራረብ ከፕሬዚዳንቱ ጥሩ ምላሽ ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

ቦር የተባለው አካባቢ በአማጽያን እጅ የወደቀ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ድንበር በሆነው አኮቦ በትናንትናው እለት ጦርነት ተከፍቷል። ዛሬ ደግሞ ማላኪ፣ ዋው እና ባንቲዩ በተባሉት አካባቢዎች ጦርነት ተከፍቷል። ባንቱዊ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጽህፈት ቤት የሚገኝበት ሲሆን፣ በርከታ የዲንቃ ተወላጆች በጽህፈት ቤቱ ግቢ ውስጥ መግባታቸው ታውቋል። በጁባ የኑዌር ተወላጆች ከዲንቃ ጎሳዎች ጥቃት ሊሰነዘር ይችላል ብለው በተመድ ጽ/ቤት ውስጥ ሲጠለሉ፣ በቤንቲዩ ደግሞ በተቃራኒው ዲንቃዎች ተጠልለዋል።

## ኢትዮጵያና ከግብፅ በአበይ ወንዝ ላይ አሁንም ስምምነት ላይ አልደረሱም ተባለ

በ2004 ዓም መገባደጃ አካባቢ የኢትዮጵያና የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አዲስ አበባ ዉስጥ ተገናኝተው የአባይ ወንዝን አስመልክቶ ለመነጋገር በተስማሙት መሠረት፣ የኢትዮጵያ፤ የሱዳንና የግብፅ የውኃ ሚኒስትሮች ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ ያቀረበው የመፍትሔ ሐሳብ ሪፖርት ተግባራዊ መሆን በሚችልበት ሁኔታ ላይ ተወያዩ። በጥቅምት ወር መጨረሻ ሱዳን ዉስጥ የተገናኙት የሦስቱ አገሮች ሚኒስትሮች በመፍትሔ ሐሳቡ ተግባራዊነት ላይ በመወያየት ቀጣይ ዉይይቶችን የሚያመቻችና የሚከታተል ኮሚቴ ለመመሥረት በሐሳብ ደረጃ መስማማታቸውን፣ ነገር ግን በኮሚቴው አባላት ስብጥር ላይ መግባባት ባለመቻላቸው ውይይቱ ተቋርጦ ለሌላ ጊዜ መተላለፉ የሚታወስ ነዉ።

የኢትዮጵያ የኮሚቴው አባላት ሙሉ በሙሉ የሦስቱ አገሮች ባለሙያዎች ብቻ መሆን አለባቸው የሚል ጠንካራ አቋም ያላት ሲሆን በሚለው በግብፅ በኩል ግን የውጭ ባለሙያዎች እንዲካተቱ አቋም በመያዙ ለዩነቶች ተፈጥረዉ ነበር። ይህንን ልዩነት ለመፍታት ከተያዘው ቀጠሮ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን የኢትዮጵያና የሱዳን የጋራ ኮሚሽን ዓመታዊ ጉባዔን ምክንያት በማድረግ ወደ ሱዳን ማቅናቱንና በወቅቱም በሦስቱ አገሮች ድርድር ላይ የሱዳን መንግሥት የኢትዮጵያን አቋም እንዲረዳ አድርጓል።የሱዳን የውኃና የኤሌክትሪሲቲ ሚኒስትር መንግሥታቸው የኢትዮጵያን አቋም ሙሉ በሙሉ ከመቀበል ባለፈ፣ በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የማግባባት ሚና እንደሚኖራት በመተማመን ሁለተኛው የሦስቱ አገሮች ድርድር ከመጀመሩ ቀናት በፊት ወደ ግብፅ ማቅናታቸውን ገልጸዋል። የሱዳን ሚኒስትር በካይሮ ቆይታቸው ከግብፅ ባለሥልጣናት ጋር በመገናኘት የኢትዮጵያን አቋም ማስረዳታቸውንና የግብፅ መንግሥት የኢትዮጵያን ሐሳብ እንደሚደግፍ ተገልጾላቸው መመለሳቸውን አስረድተዋል።

ግብፅ የህዳሴው ግድብ ከፍታ ዝቅ ይበል በሚል ሐሳቧና የዓባይ ተፋሰስ አገሮች ማለትም የግብፅና የሱዳን የውኃ ደኅንነትና ፍላጐት ሙሉ በሙሉ መከበር አለበት በሚለዉ አቋማ አሁንም እንደጸናች ሲሆን በተላይ በኢትዮጵያ በኩል በፍጹም ተቀባይነት በሌለዉ "የቅኝ ግዛት የውኃ ኮታዬ ይከበር" በሚለዉ አቋሟ እንደጸናች ነዉ። እነዚህ ሀሳቦች ኢትዮጵያ በጭራሽ የምትቀበላቸዉ ሀሳቦች አይደሉም ያሉት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ዘርፍ ሀላፊ አቶ ፈቅ፣ በዚህና በሌሎች የመወያያ ነጥቦች ላይ ትኩረት በማድረግ ውይይቱ በሦስቱ አገሮች መካከል ለወደፊትም እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

## ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ሕዝብ ያዋጣው 5.7 ቢሊየን ብር ነው ተባለ

ሙሉ በሙሉ የፋይናንስ ምንጩን በአገር ዉስጥ ቁጠባና ከህዝብ በሚገኝ መዋጮ ላይ ብቻ ተማምኖ ስራዉን የጀመረዉ የህዳሴዉ ግድብ ፕሮጀክት እስካሁን ድርስ ከህዝብ ያገኘዉ ገንዘብ 5. 7 ቢሊዮን ብር ብቻ ወይም ባጠቃላይ ፕሮጀክቱ ይፈጃል ከተባለዉ 6.5% ብቻ መሆንኑን አንድ ከፍተኛ የአገዛዙ በለስልጣን ተናገሩ። ባለፉት ሶስት ዓመታት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ከሕዝብ የተዋጣው ገንዘብ ከ10 ቢሊየን ብር በላይ መሆኑ በመንግስት የመገናኛ ብዙሀን ሲነገር ቢቆይም አንድ ባለስልጣን ግን ትክክለኛው አሀዝ 5 ነጥብ 7 ቢሊየን ብር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽ/ቤት የአቶ በረከት ስምኦን ምክትል የሆኑት አቶ ዛዲግ አብርሃን ጠቅሶ መንግስታዊው አዲስ ልሳን ጋዜጣ እንዳሰፈረው ባለፉት ሶስት ዓመታት ከህዝብ የተዋጣው ገንዘብ 5 ነጥብ 7 ቢሊየን ብር ብቻ ነው። የዋጋ ግሽበትን ሳይጨምር ከ85 ቢሊየን ብር ባላይ ይፈጃል የተባለው የአባይ ግድብ ግንባታ ማከናወኛ ሕዝቡ እስካሁን ማዋጣት የቻለው ገንዘብ መጠን አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ቃል የገቡ በርካታ ባለሃብቶች በቃላቸው መሰረት መዋጮውን አለማስገባታቸው ትልቅ ችግር መሆኑ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አመልክተዋል።

የመንግስት ሠራተኞችና ሌሎች ደመወዝተኞች ገንዘቡ ከደመወዛቸው የሚቆረጥ በመሆኑ በትክክል መክፈል የቻሉት እነዚሁ ወገኖች ብቻ ናቸው ተብሎአል። ይህም ግድቡ በተያዘለት የጊዜ ገደብ መሰረት ለማጠናቀቅ የፋይናንስ ችግር ማነቆ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ የሚያመላክት ሆኖአል። በተያያዘ ዜና ከአባይ ግድብ ጋር በተያያዘ በግዳጅና በፍላጎት ከሕዝብ የሚሰበሰብ ገንዘብ ለታቀደለት ኣላማ በትክክል ስለመዋሉ የሚያረጋግጥ ግልጽ የሆነ አሰራር በመንግስት በኩል እስካሁን አለመዘርጋቱ አሳሳቢ መሆኑን ለጉዳዩ ቀርበት ያላቸው ወገኖች አስታውቀዋል። ሕዝቡ ከደመወዙ በግዳጅና በፍላጎት ቦንድ እንዲገዛ ሲደረግ መቆየቱን ያስታወሱት እነዚሁ ወገኖች ሕዝቡ ምንያህል በመዋጮ መልክ እንደተሰበሰበና በምን መልኩ ስራ ላይ እየዋለ እንደሆነ የተረጋገጠ መረጃ አለመያዙ አሳሳቢ ነው ተብለዋል።

የስርዓቱ ቁንጮዎች ከላይ እስከታች በሙስናና ብልሹ አሰራር ውስጥ መዘፈቃቸውን በተረጋገጠበት በዚህ ወቅት ከህዝብ የሚሰበሰብ ገንዘብ በትክክል ስራ ላይ ይውላል ብሎ ለመገመት አዳጋች መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ ወገኖች መንግስትም ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልክ የሕዝብ ገንዘብ ስለማስተዳደሩ ማረጋገጫ እያቀረበ አለመሆኑ አሳሳቢ ነው ሲሉ አክለዋል።

ግድቡ በመጋቢት ወር 2003 ዓ.ም በይፋ የመሰረት ድንጋ ተጥሎ ከተጀመረ ወዲህ በርካታ የመንግስትና የግል ሰራተኞች፣ ባለሃብቶችና ሌሎች ወገኖች ገንዘብ ሲያዋጡ መቆየታቸውን ያስታወሱት እነዚሁ ወገኖች ሌላው ቀርቶ የቦንድ ሰርተፊኬት ያገኙ ሰራተኞች ቁጥር ብዙ አለመሆኑና ገንዘቡም በትክክል መቼ እንደሚመለስ አለመታወቁን አስታውሰዋል። ከምንም በላይ ሳይወድ በግድ ያዋጣው ሰፊ ሰራተኛ ገንዘቡ በትክክል ስራ ላይ እየዋለ መሆኑን እንኳዋን የሚያውቅበት መንገድ አለመኖሩ የስርዓቱ ቁንጮዎች የሕዝብን ገንዘብ በግልጽ ለማስተዳደር ፍላጎት እንደሌላቸው የሚሳይ ነው ብለዋል።

የግድቡን አብዛኛውን ስራዎች የሚሰሩት ሳሊኒ የተባለው የጣሊያን ኩባንያና የህወሀት እንዲሁም ከህወሀት ጋር በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው። በመከላከያ ስም ከፍተኛ የህወሀት ጄኔራሎች ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የወያኔ አገዛዝ የአንድ ለአምስት አደረጃጀትን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በቤተሰብ ፖሊስ ማቋቋሚያ ቅጹ ላይ " የመራች የቤተሰብ ፖሊስ ወይም ተወካይ ስም፣ የቤተሰብ ብዛት፣ ስልክ ቁጥር፣ የተወካይ ፊርማ፣ መንደር ወይም ልዩ ቦታ፣ የብሎክ ቁጥር፣ ብሄርና መግለቻ የሚሉ ጥያቄዎች ተካተዋል።በተመሳሳይ ዜናም የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በከተማው ውስጥ በሚገኙ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሒደት በጥራት ለማከናወን ይረዳል በማለት ‹‹ኮማንድ ፖስት›› የተሰኘና ሌሎች ተጨማሪ አደረጃጀቶች በማስተዋወቅ ላይ መሆኑን ሪፖርተር ዘግቧል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በከተማው ከሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለተጠሩ ርዕሳነ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮችና ከሁሉም ክፍላት ከተሞችና ወረዳ ጽሕፈት ቤቶች ለተወከሉ ኃላፊዎች በአዲሶቹ አደረጃጀቶች ዙሪያ ገለጻ አድርጓል፡፡ በቅርቡ ወደ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ይወርዳል ከተባለው የኮማንድ ፖስት አደረጃጀት በተጨማሪ፣ ‹‹ትራንስፎርሜሽን ፎረም›› እና ‹‹የልማት ቡድን›› የሚሰኙ አደረጃጀቶችም እንደሚተዋወቁ ጋዜጣው ዘግቧል።

‹‹ኮማንድ ፖስት›› አደረጃጀት ዋና ተግባሩ ትምህርት ቤቶችን ከሕዝባዊና ከመንግሥት ክንፎች ጋር ማስተባበር እንደሆነ የዘገበው ጋዜጣው ፤ የ‹‹ትራንስፎርሜሽን ፎረም›› እና ‹‹የልማት ቡድን›› የተባሉት አደረጃጀቶችም በየትምህርት ቤቱ በሚገኙ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን፣ ‹‹አንድ ለአምስት›› በሚል ስያሜ የተጀመረውን አደረጃጀት ለማጠናከርና ለማስቀጠል ጠቃሚ መሆናቸው ተመልክቷል። ላለፉት ጥቂት ዓመታት በ‹‹ግንባር ቀደም›› አደረጃጀት በኋላም በ‹‹ተጓዳኝ›› አማካይነት የተከናወነው ሥራ የታሰበውን ውጤት ማምጣት አለመቻሉ ግልጽ መሆኑ በመታወቁ ‹‹ኮማንድ ፖስት›› የተባለውን አደረጃጃት ለማስተዋወቅ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ተገልጿል።

መንግስት የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ‹‹ተጓዳኝ›› የሚባለውን አደረጃጀት ማምጣቱን ቢገልጽም፣ አንዳንድ መምህራን ግን መንግሥት መምህራኑን ‹‹ለመጠርነፍ›› ሲል ያመጣቸውና ‹‹ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን አላስፈላጊ መሣሪያ›› ነው ሲሉ ውድቅ ያደርጉታል።ጋዜጣው አያይዞም፣ ‹‹አደረጃጀት በዛ፣ እኛም ለማስፈጸም እየተቸገርን ነው፤›› በማለት ርዕሰ መምህራን ለትምህርት ቢሮ ኃላፊው መግለጻቸውን ዘግቧል። ባለስልጣኑ ግን መምህራን የማሳመን ስራ መስራት ይኖርባቸዋል በማለት የርእሰ መምህራኑን ቅሬታ ሳይቀበሉት ቀርተዋል። ጋዜጣው ያነጋገራቸው መምህር ስለአደረጃጀት መብዛት ተጠይቀው ‹‹አደረጃጀት በማለት መንግሥት በየትምህርት ቤቶቻችን የሚያመጣብን አሠራሮች ብዙ ጊዜ መምህራንን ከማባሳጨት አልፎ የትምህርት ጥራትን የባሰ እየገደለ ነው፤›› በማለት መልሰዋል። መንግስት የአገሪቱን ህዝብ በመላ በአንድ ለ አምስት አደረጃጀት ለመቆጣጠር ያስባል በሚል ወቀሳ እቀረበበት ቢሆንም፣ ኢህአዴግ በ9ኛው መደበኛ ጉባኤ በአደረጃጀቱ እንደሚገፋበት ውሳኔ አሳልፎአል።

## ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ሕዝብ

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

የሚያንቀሳቅሱት እና ከፍተኛ ሙስና እንደሚፈጸምበት የሚነገርለት ሜቴክ እየተባለ የሚጠራው ድርጅት በግንባታው ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረገ ነው። የወ/ሮ አዜብ መስፍን የቅርብ የስጋ ዘመድ የሆኑት ግለሰብ ንብረት የሆነው ወርኪድ የተባለው ድርጅትም እንዲሁ በእቃዎችና በማሽነሪ አቅርቦት በኩል ከፍተኛ ስራዎች ተሰጥቶት እየሰራ ነው።

## ዕንባሽ ተናገረ!

ዘለላ ዘለላ ደብ ደብ በሚለው፤
ጉንጭሽን ሽርሽሮ ቁልቁል በሚፈሰው፤
ሳግ እንቅ እድርጎ በሚተናነቅሽ፤
በ’ንባሽ እያጠቀስኩ ስንኝ ቋጠርኩልሽ፤
ቃል ኪዳን ነውና አንብቢው አደራሽ::

ዕንባሽ ተናገረ ! ሆሄያት ቆጠረ፤
ውስጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ፤
ቃላትን አምጦ ስንኞች ቋጠረ፤
ምሥጢሩን አወራ - መደበቁ ቀረ::

አይምሮሽን ነድሎ - ልብሽን ሰርስሮ፤
ቆፍሮ ዐይኖችሽን - ጉንጭሽን ሽርሽሮ፤
አንጀትሽን ሞሽልቆ - ጨጓራሽን ልጦ፤
ቁልቁል በሚወርደው ደረትሽን አቋርጦ፤
ሳግ እንቅ እድርጎ በሚተናነቅሽ፤
በሚፈልቀው ኩሬ - እያጠቀስኩ በንባሽ፤
ጥቂት ቃል ጻፍኩልሽ፤ አንብቢው አደራሽ::

ዕንባሽ ተናገረ! ፊደላት ቆጠረ፤
ውስጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ፤
ቃላትን አምጦ ስንኞች ቋጠረ፤
ምሥጢሩን አወራ - ጮሆ ተናገረ::

ሃዘንሽ ፈንክቷት ብዕሬ ቆሰለች፤
ከግራ ወደቀኝ እየተወራጨች፤
ድምጿን ከፍ አድርጋ - እሪ ብላ ጮኸች፤
ባንቺ ዕንባ ተጠምቃ - ማተቧን ቋጠረች፤
ፊትሽን ለማበስ - ሮጠች ተሯሯጠች፤
ሃቅሽን አውጥታ - ጻፈች ቸከቸከች::

ያይኖችሽን ኩሬ ነድሎ በሚፈልቀው፤
ጅረት እንደ ዓባይ አቀብ በሚፈሰው፤
በሚገነፍለው እያጠቀስኩ በ’ንባሽ፤
ይችን ጥቂት ስንኝ ላንቺ ቋጠርኩልሽ፤
በ’ንባ የጨቀየ የራሰ ነው ብለሽ፤
እንዲትጠየፊ አንብቢው አደራሽ ::

ዕንባሽ ተናገረ ! ፊደላት ቆጠረ፤
ውስጥሽን ፈልፍሎ እየመረመረ፤
ቃላትን አምጦ ስንኞች ቋጠረ፤
ምሥጢሩን አወራ - ትንቢት ተናገረ ::

እናም:
ጻፍኩልሽ ! ጻፍኩልሽ ! እህቴ ልንገርሽ፤
እያጠቀስኩ በ’ንባሽ፤
ተመኝቼ ሳቅሽን ዳግም እንዲታለቅሽ፤
እህቴ!

አሥራዮው (ከፈረንሳይ)

በሳውዱ አረቢያና፤ በመላ አረብ አገራት፤ ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ፤ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ የተቋጨች :: ጥቅምት 21/2006 ዓ.ም (October 31/2013)